# የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት

## መመሪያ ቁጥር 1117/2018

## ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች አወጋገድ መመሪያ

**ህዳር / 2018 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ/ ኢትዮጵያ**

በአዋጅ ቁጥር 1354/2017 አንቀጽ 10(26) ላይ አገልግሎቱ ለሌሎች ተቋማት ለሚሰጠው የማስወገድ አገልግሎት የሚያስከፍለው ታሪፍ በመመሪያ እንዲወስን ስልጣን የሰጠው በመሆኑ፣

የማስወገጃ ማዕከሉ ወጭውን በራሱ እንዲሸፍንና ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ተገቢ የሆነውን ታሪፍ ለማስከፈል በማስፈለጉ፣

በአቅርቦት ሰንሰለቱ በየደረጃው ባሉ ተቋማት አቅርቦቱን የማጠናከርና ብክነትን የመቀነስ ስራዎች የሚከናወኑ ቢሆንም ብክነትን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት የማይቻል ስለሆነና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው እና የተበላሹ መድኃኒቶች በአግባቡ ማስወገድ ተገቢ በመሆኑ፣

በተለያየ ምክንያት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ ጥቅም የማይሰጡ መድኃኒቶችን ለአካባቢ ጠንቅ ሳይሆኑ የሚወገዱበትን ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በማስወገጃ ማዕከሉ ሊወገዱ የሚገባቸውን ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች በተመለከተ አግባብነት ያለው አያያዝ፣ አስተሻሸግና፣ የርክክብ ስርዓት ለመዘርጋት በማስፈለጉ፣

አገልግሎቱ በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎትና ፈንድ ማቋቋሚያ በአዋጅ ቁጥር 1354/2017 አንቀጽ 28 (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ መመሪያ "**ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 1117/2018**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤-

1/ "**ጥቅም ላይ የማይውል መድኃኒት**" ማለት የጥራት ጉድለት ተገኝቶበት ወይም በመሰበሩ ወይም በመጎዳቱ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜው በማለፉ ምክንያት ወይም በሌላ እንከን ምክንያት ጥቅም ላይ መዋል የማይችል ማለት ነው፤

2/ "**ጥቅም ላይ የሚዉል ተረፈ ምረቶች**" ማለት መልሶ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብአቶች ማለትም የማሸጊያ ካርቶኖች፣ ላስቲኮች፣ ብረት ነክ ነገሮች፣ አልሙኒየም፣ ጠርሙሶች ፓሌቶች እና የመሳሰሉትን ያካትታል፤

3/ "**ጥቅም ላይ የማይውል ተረፈ ምርት**" ማለት ጥቅም ላይ የማይውል መርዛማነት ካለው መድኃኒት ጋር ንክኪ ያለው ማሸጊያ ካርቶን፣ፕላስቲክ፤ ወረቀትና ሌሎች ተመልሰው ጥቅም ላይ የማይውሉ በሰው፣በእንስሳና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያመጡ ናቸው፤

4/ "**የማስወገጃ ማዕከል**" ማለት በአገሪቱ የተለያይዩ ከተሞች ላይ የማቃጠያ ኢንሲኔሬተሮች የተገነቡለት የራሳቸዉ ጊዚያዊ ማከማቻ መጋዘን እና የተደራጀ ሰው ሀይል ያላቸዉ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶችንና ሌሎች ተያያዥ ግብዓቶችን ለአካባቢ ጠንቅ ሳይሆኑ በተገቢው መንገድ የማስወገድ ስራን የሚያከናዉኑ የአገልግሎቱ የማስወገጃ ማዕከላት ናቸዉ፤

5/ "**የማስወገጃ የምስክር ወረቀት**" ማለት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው በማለፉ ምክንያት ወይም በሌላ ምክንያት እንዲወገዱ የተደረጉ ግብዓቶችን ዝርዝር መግለጫ የያዘ በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰነድ ማለት ነው፤

6/ "**የማሸጊያ ቁሳቁስ**" ማለት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው በማለፉ ወይም በሌላ ምክንያት የሚወገዱ ወይም የሚቃጠሉ ግብዓቶችን በአግባቡ ለመያዝ ወይም ለማሸግ የሚያገለግል እንደ ፕላስቲክ ከረጢት፣ ካርቶን፣ ፕላስተር፤ማሰሪያ ገመድ የመሳሰሉት ማለት ነው፤

7/ "**የመጠቀሚያ ጊዜ**" ማለት በአምራች ድርጅቱ የሚሰጥ የጊዜ ገደብ ሆኖ መድኃኒቱ ጥቅም ላይ የሚውልበትን እና ጥቅም የማይሰጥበትን ጊዜ የሚወስን ነው፤

8/ "**የክልል ጤና ተቆጣጣሪ**" ማለት በምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2019 መሰረት የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅንና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ህጎችን በክልል ደረጃ ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል መንግሥት አካል ነው፤

9/ **"የግል የጤና ተቋም"** ማለት በግሉ ዘርፍ መዋዕለ ነዋይ የተቋቋሙ ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ማለት ነው፤

10/ **"የመንግስት ጤና ተቋም"** ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስታት ባለቤትነት የሚተዳደር የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

11/ **"የበላይ አመራር"** ማለት ተቋሙን በበላይነት የሚመሩትን ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችን ለማለት ነው፡፡

12/ **"መንግስታዊ ያልሆኑ የጤና ድርጅቶች"** ማለት በተለያየ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ የተቋቋሙ ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ማለት ነው፤

13/ **"ተቆጣጣሪ ባለስልጣን"** ማለት አግባብነት ያለው የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን እንደአስፈላጊነቱ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ይጨምራል፤

14/ **"ጊዜያዊ ማከማቻ መጋዘን"** ማለት ጥቅም ላይ የማይዉሉ መድኃኒቶችና ሌሎች ግብአቶች እስከሚወገዱ ድረስ ሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ የሚከማቹበት መጋዘን ነው፡፡

15/ **"አገልግሎት"** ማለት የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ማለት ነው፤

16/ **"ቅርንጫፍ"** ማለት በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ስር የሚተዳደሩና ለጤና ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው፤

17/ በአዋጁ ላይ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላቶችና ሐረጎች በዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚደረገው በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ዋና መስሪያ ቤት እና በማስወጋጃ ማዕከላት፣ በቅርንጫፎች እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ አገልግሎት ለማግኘት በሚፈልጉ ተቋማት ላይ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ጥቅም ላይ የማይውሉ ግብዓቶች መለየት፣ ማሸግ እና ማጓጓዝ</u>

## 4. <u>መለየት</u>

1/ የመጀመሪያ የመለየት ስራ የሚከናወነው ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች ከሚገኙበት ተቋም እና የአገልግሎቱ መጋዘኖች ይሆናል፤

2/ ጥቅም ላይ የማይውሉ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው፤ የተጎዱ፤ የጥራት ችግር ያለባቸውን መድኃኒቶች በዓይነትና በአገልግሎት ጊዜ በመለየት በተለየ ስፍራ መቀመጥ አለባቸው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተገለጸው መሰረት በልየታው ላይ የሚሳተፉ ሰራተኞች አስፈላጊውን የአደጋ መከላከያ አልባሳት እና ቁሳቁሶችን መጠቀም አለባቸው፤

4/ ልየታው የሚከናወንበት ስፍራ መድኃኒቶቹን ለመለየት የሚያስችል በቂ ስፍራና አየር የሚገባበት መሆን ይኖርበታል፤

5/ ልዩ ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች በጥንቃቄ ከተለዩ በኂላ በተለየ ስፍራ ተቆልፈው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

6/ በባህሪያቸው ተቀጣጣይ እና በቀላሉ እሳት የሚፈጥሩ ኬሚካሎች፤ የካንሰር መድኃኒቶች በጥንቃቄ መለየት አለባቸው፤

7/ ፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች ይዘታቸው በዱቄት፣ጠጣርና ፈሳሽ ባህሪ ያላቸው ግብአቶች እንደየ ባህሪያቸው ተለይተው ለየብቻ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

8/ የመለየቱ ሂደት መልሶ ጥቅም ላይ የሚዉሉ እና የማይውሉ፣ ጥቅም ላይ የማይዉሉ ከሆነ ተስማሚ የሆነዉን የማስወገጃ መንገድ መምርጥ እና የሚወገዱትን ምርቶች ዝርዝር ከተለዩ በኂላ በስም፣ በመለኪያ፣ በመጠን፣ የማሸጊያ አይነት፣ መለያ ቁጥር፣ አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን፣ የተመረተበት ቀን፣ አምራች፣ የተመረተበት ሀገር፣ የምርቱ ዋጋ እና ግብአቶቹን እንዲወገድለት የጠየቀው ተቋም ወይም የአገልገሎቱ መጋዘን በግልጽ መቀመጥ አለበት።

9/ በማስገኛ ማዕከላቱ ሊወገዱ የሚችሉና የማይችሉ መድኃኒቶችና ሌሎች ተያያዥ ግብአቶች በኢትዮጵያ መድኃኒትና ምግብ ባለስልጣን መመሪያ መሰረት ሊለዩ ይገባል፤

## 5. <u>ማሸግ</u>

1/ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶችና ሌሎች ግብዓቶች እንደየ ባህሪያቸው (ተቀጣጣይ፣ ፈሳሽ፣ ጠጣር፣ ዱቄት፣ ወዘተ) ለየብቻ መታሸግ አለባቸው፤

2/ ሊወገዱ የተዘጋጁ መድኃኒቶችና ሌሎች ግብአቶች በአንድ ላይ በሚታሸጉበት ጊዜ በእሽጉ ውስጥ የሚገኙ ግብአቶች አይነት፤ ብዛት እና የግብአቶቹን ባህሪ ተጠቅሶ በማሸጊያው ላይ መለጠፍ አለበት፣

3/ ፀረ-ካንሰር መድኃኒቶች እና ሌሎች መርዛማ የሆኑ መድኃኒቶች በሀምራዊ፣ ራዲዮ ፋርማሲዉቲካልስ በቡናማ ቀለም የሚለዩ ሲሆን ሌሎች ግብዓቶች ግን በሰማያዊ ቀለም እንዲለዩ በማድረግ መታሸግ አለባቸው፤

## 6. <u>ማጓጓዝ</u>

1. ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶችና ሌሎች ተያያዥ ግብዓቶችን የማስወገድ አገልግሎት የሚፈልጉ ተቋማት ወይም የአገልግሎቱ ቅርንጫፎች ወደ ማስወገጃ ማዕከላት በማጓጓዝ እና ለማስወገጃ ማዕከላት ማስረከብ ያለባቸው ቢሆንም ከተቋማት ጋር በሚገባው የማስወገድ አገልግሎት ውል መሰረት የሚሰራ ይሆናል። የአገልግሎቱ ቅርንጫፎች የማጓጓዝ እና ለማስወገጃ ማዕከላት የማስረከብ አገልግሎት እንደአስፈላጊነቱ በጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች የአወጋገድ ስርዓት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማስተባበር ሊሰራ ይችላል።
2. ጥቅም ላይ የማይውሉ ግብዓቶች ወደ ማስወገጃ ማዕከላት በሚጓጉዙበት ወቅት በሸፍን ተሽከርካሪ ወይንም በሸራ ተሸፍነዉ በጥንቃቄ መጓጓዝ ይኖርባቸዋል፤

3. የሚወገዱ ግብአቶች ወደ ማስወገጃ ማዕከል በክፍል ሶስት አንቀጽ 9 መሰረት ታሽገው መድረስ አለባቸው፤

## ክፍል ሶስት

## ጥቅም ላይ የማይውሉ ግብዓቶች መረከብ፣ ማከማቸት፣ ማስወገድ፣ ተረፈ ምርቶች የማስተዳደር እና የምስክር ወረቀት መስጠት

7. **መረከብ**

1/ ማንኛዉም የማስወገድ አገልግሎት ፈልጎ ወደ አገልግሎቱ የማስወገጃ ማዕከል የሚመጣ ደንበኛ ወይም ቅርንጫፍ ስለሚወገደዉ ግብአት በአይነት፣ በመለኪያ፣ በመጠን፣ በአምራች፣ በመለያ ቁጥር፣ በሽረት ጊዜ፣ በዋጋ እና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች ተዘርዝረዉ በአካባቢው ካለዉ የመድኃኒትና ምግብ ባለስልጣን ማረጋገጫ የተሰጠበትን ፍቃድና የመጠየቂያ ደብዳቤ ይዞ መቅረብ አለበት፤

2/ ማስወገጃ ማዕከሉ ሊወገዱ የመጡ ግብዓቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ መሆናቸውንና በማዕከሉ መወገድ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤ እንዲሁም ከማስወገድ አሰራር ስርዓት ውጭ የሆኑ ግብዓቶች ከመጡ ወደ መጡበት እንዲመለሱ መደረግ አለባቸው፤

3/ አገልግሎት ፈላጊው ተቋም ወይም ቅርንጫፍ ከህጋዊ ወጪ ደረሰኙ በተጨማሪ እንዲወገድለት ስለመፈለጉ የሚገልጽ በተቋሙ ወይም በቅርንጫፉ ሃላፊ የተፈረመ ማረጋገጫ ደብዳቤ አባሪ ማድረግ አለበት፤

4/ የርክክብ ስርዓቱ በመረከቢያ መጋዘን አስረካቢና ተረካቢ ባሉበት በወጪ ሰነድ መሰረት ርክክብ ይፈፀማል፤ የማስረከቢያ ሰነዶቹ ላይ ያለው ግብዓት በዓይነት፣ በመለያ ቁጥር እና በመጠን በአካል ካለው ግብዓት ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ተረጋግጦ ገቢ በማድረግ የገቢ ሰነድ ተቆርጦ ለአስረካቢዉ አካል መሰጠት አለበት፤

5/ የማስወገጃ ማዕከሉ ሊወገዱ የመጡትን ግብአቶች በመድኃኒቱ ስም፣ አይነት፣ መለኪያ፣ ብዛት፣ በመለያ ቁጥር፣ የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የሚወገድበት ምክንያት፣ የአምራች ስም፣ የተመረተበት ሀገር እና የዋጋ ዝርዝር መሰረት መረካከብ ይኖርበታል፡፡

8. **ማከማቸት**

1/ የርክክብ ስርዓቱ ከተፈጸመ በኂላ የሚወገዱ ግብዓቶች ከመረከቢያ ስፍራ ወደ ጊዜያዊ ማከማቻ እንዲቀመጡ ይደረጋል፤

2/ ግብአቶቹ በማከማቻ መጋዘን ውስጥ ሲቀመጡ እንዲወገድለት የጠየቀው ተቋም ወይም ቅርንጫፍ ስም ተጽፎበት መቀመጥ አለበት፤

3/ በባህሪያቸው ተቀጣጣይ እና በቀላሉ እሳት የሚፈጥሩ ግብዓቶች በተለየ ስፍራ በጥንቃቄ መከማቸት ይኖርባቸዋል፤

4/ ወደ ጊዜያዊ ማከማቻ መጋዘን ከተፈቀደለት ሰው ውጭ መግባት የለበትም፡፡

9. **ማስወገድ**

1/ የማስወገጃ ማዕከሉ እቅድ አውጥቶ የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ወይም የክልል ጤና ተቆጣጣሪ በተገኘበት እንዲወገድ ያደርጋል፤

2/ ተለይተው ወደ ማስወገጃ ማዕከሉ የመጡ መድኃኒቶችና ሌሎች ግብዓቶች በማዕከሉ ኢንሲነሬተር መወገድ የሚችሉ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት፤

3/ ወደ ማስወገጃ ማዕከሉ የመጡ ግብዓቶች በውጪኛው ማሸጊያ ላይ የተቀመጠው ዝርዝር መረጃ ከውስጠኛው ጋር ተመሳሳይ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

4/ የሚወገዱት ግብዓቶች ከአገልግሎቱ ዉጭ ማለትም ከጤና ተቋማት የመጡ ከሆነ ክፍያ ስለመክፈሉ ወይም በቅድሚያ ክፍያ ውል መሰረት ስለመስተናገዱ መረጋገጥ አለበት፤

5/ የማስወገድ አገልግሎት ፈልገዉ የሚመጡ ደንበኞች ከአገልግሎቱ ማስወገጃ ማዕከል ጋር ወቅቱን የጠበቀ ዝርዝር የዉል ስምምነት ሊኖራቸዉ ይገባል፤

6/ ጥቅም ላይ የማይዉሉ ግብዓቶች ከተወገዱ በኋላ የሚቀረው ተረፈ ምርት ወይም ዓመድ በተገቢዉ ሁኔታ መወገድ አለበት፡፡

10. **መልሶ ጥቅም ላይ ስለሚዉሉ ተረፈ ምርቶች**

መልሶ ጥቅም ላይ የሚዉሉ ተረፈ ምርቶችን ለማስተዳደር በአገልግሎቱ የበላይ አመራሮች ውሳኔ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

11. **የምስክር ወረቀት**

1/ ማስወገጃ ማዕከሉ ጥቅም ላይ የማይውሉ ግብዓቶች ከተወገዱ በኃላ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከመድኃኒትና ምግብ ባለስልጣኑ መቀበል አለበት፤

2/ ማስወገጃ ማዕከሉ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደተቀበለ፤ ግብአት ለተወገደለት ቅርንጫፍ ወይም ተቋም በውሉ መሰረት መስጠት አለበት፤

3/ መድኃኒትና ምግብ ባለስልጣን የሚሰጠው የምስክር ወረቀት በአግባቡ ፋይል መደረግ አለበት፤

## ክፍል አራት

## የአገልግሎት ዋጋ አወጣጥ እና የሂሳብ አሰባሰብ

12. **የአገልግሎት ጥቅም ላይ የማይውሉ ግብዓቶች ዋጋ አወጣጥ መርሆዎች**

1/ ለማስወገጃ ማዕከሉ መድኃኒት ላስወገደበት የሚከፈለውን የማስወገድ የአገልግሎት ታሪፍ የሚተምነው ጥቅም ላይ የማይውሉ ግብአቶችን ለማስወገድ የሚወጣውን ወጭ እና የማስወገጃ ማሽኖችን ዋጋ በ10 ዓመታት ውስጥ ለመመለስ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በዚህ መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፤

2/ አንድ ኪሎ ግራም ለማስወገድ የሚጠይቀው ቀጥተኛ ወጪዎች፡-

ሀ) የማስወገጃ ማሽኖች የእርጅና ቅናሽ

ለ) የሰራተኛ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም፣

ሐ) የኤሌክትሪክ እና የውሀ ወጪዎች፣

መ) የነዳጅ ፍጆታ፣

ሠ) የጥገና እና የመለዋወጫ ወጪዎች፣

ረ) የኢንሹራንስ ወጪዎች፣

ሰ) የተረፈ ምርት ማስወገጃ ወጪዎች፣

ሸ) የመጫኛና ማውረጃ ወጪዎች፣

ቀ) ለአደጋ መከላከያ የሚወጡ ወጪዎች፣

በ) ለቅድመ ተጋላጪነት ለመከላከል የሚወጣ ወጪ፣

ተ) የማሸጊያ፤ የመለየት ወጪዎች፣

ቸ) የጊዜያዊ ማቆያ መጋዘን ወጭዎች፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸው የቀጥተኛ ወጪዎች መጠን ወቅታዊ የገበያ ሁኔታን ያማከለ መሆን ስላለበት በየዓመቱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ ዓመት ባጠረ ጊዜ ውስጥ በሚካሄድ የዋጋ ማሻሻያ ዳሰሳ ጥናት መሰረት በአገልግሎቱ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማፀደቅ የሚከለስ ይሆናል።

4/ አንድ ኪሎ ግራም ለማስወገድ የሚጠይቀው ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች፡-

ሀ) የሰራተኛ ውሎ አበል ወጪዎች፣

ለ) ስልክና በይነ-መረብ ወጪዎች፣

ሐ) የቢሮ አገልግሎትና አስተዳደራዊ ወጪዎች፣

መ) የህዝብ ግንኙነት አገልግሎት ወጪዎች፣

ሠ) የባንክ አገልግሎት ወጪዎችን

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተገለጸውን ቀጥተኛ ያልሆነ ወጪ መጠን የቀጥተኛ ወጪ 15% ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (4) የተገለጸው የቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ወጪን ሽፍኖ ጥቅም ላይ ለማይውል መድኃኒት የማስወገድ አገልግሎት የሚከፈለው ታሪፍ 15% ነው፣

## ክፍል አምስት

## የክትትናና ግምገማ ስርዓት

13. **የክትትልና ግምገማ ስርዓት**

1/ በአገልግሎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች እና ተያያዥ ግብአቶች የአወጋገድ ስርዓት አስተዳደር ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች በየወቅቱ እየተሻሻሉ እንዲሄዱና ዘመናዊ አሰራር እንዲሰፍን ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎች በመቅረጽ አፈጻጸሙን መለካትና የማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል፤

2/ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች እና ተያያዥ ግብአቶች የአወጋገድ ስራዎች አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ ስርዓት በአገልግሎቱ የእቅድ ክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ መሰረት መሰራት አለበት፤

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. **የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች**

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

15. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ የሚሻሻል ሲሆን የመመሪያው ክፍል አምስት የወቅቱን የገበያ ሁኔታ በማጥናትና የዋጋ ትመና በመስራት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

16. **የመመሪያው ተፈጻሚነት**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በአገልግሎቱ ድህረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ህዳር/ 2018 ዓ.ም

አብዱልቃድር ጋልጋሎ(ዶ/ር)

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት

ዋና ዳይሬክተር